# የOST (ከትምህርት ጊዜ ውጪ ፕሮግራም) ማስፋፊያ አስፈላጊነት

## እኤ 2025

ምንም እንኳን ከመደበኛ ትምህርት በኋላ የሚደረጉ ፕሮግራሞች ለልጆች እና ቤተሰቦች ጉልህ ጥቅሞችን እየሰጡ የሚገኙ ቢሆንም፣ በርካቶች አሁንም ከፍተኛ ወጪ፣ ውስን ተገኝነት እንዲሁም የትራንስፖርት ችግሮችን ጨምሮ ሌሎች የተደራሽነት ተግዳሮቶች እያጋጠሟቸው ይገኛሉ። የኮቪድ-19 ወረርሽኝ መከሰቱ የሠራተኛዎች እጥረት እንዲፈጠር እና የፕሮግራም አቅም እንዲቀንስ በማድረጉ እነዚህን ተግዳሮቶች አባብሷቸዋል። ሁኔታዎች ወደነበሩበት ተመልሰው በአካል ቢሮ ተገብቶ ወደሚሠራበት እና ትምህርት ቤት ወደሚገባበት ጊዜ ላይ ሲደረስ ፍላጎት የጨመረ ቢሆንም፣ ብዙ ቤተሰቦች ግን ሲፈልጉ የነበሩትን ከመደበኛ ትምህርት ጊዜ በኋላ የሚሰጡ የእንክብካቤ አገልግሎቶች ሳያገኙ ቀርተዋል።

ስፕሪንግ (ጸደይ) 2023 ላይ City Council (የከተማው ምክር ቤት) የCambridge ከተማ አስተዳደር ከመደበኛ ትምህርት በኋላ የሚደረጉ ፕሮግራሞችን ማስፋፋት የሚችልባቸውን መንገዶች በማግኘት፣ "Cambridge ውስጥ ያለ የፕሮግራሙ አካል ለመሆን የጠየቀ ልጅ በሙሉ" ቦታ እንዲኖረው እንዲያደርግ የሚያስችል አቅም እንዲገነባ የሚያዝ የፖሊሲ መመሪያ አስተላልፏል። የCambridge አስተዳደር ከCambridge Public Schools ጋር በመተባበር ይህ ጥናት በWithInsight፣ Resonance Data Collective እና Agenda for Children OST መሪነት እንዲካሄድ አድርጓል።

ይህ **ሪፖርት** በዚህ የአንድ ዓመት ማህበረሰብ-መር ጥናት የተገኙ ግኝቶችን እና ምክረ ሀሳቦችን ያቀርባል።

# *OST* ለልጆች ትምህርት አሰጣጥ እና ለወጣቶች እድገት ወሳኝ ነው

## እኔ 2025

እንክብካቤ ሰጪዎች ከመደበኛ ትምህርት በኋላ ስለሚደረጉ ፕሮግራሞች አስፈላጊነት እና በተማሪዎች ትምህርት አሰጣጥ እና በልጆች እድገት ላይ ያላቸውን በርካታ ጠቀሜታዎች በአጽንዖት ተናግረዋል። እንዲያውም አስተያየት ከሰጡ እንክብካቤ ሰጪዎች መካከል 51% የሚሆኑት ተጨማሪ የትምህርት ድጋፍ እና የቤት ሥራ እገዛ አንድን ፕሮግራም ለመምረጥ ዋናዎቹ ምክንያቶች መሆናቸውን ገልጸዋል። በተለይም የመጀመሪያ ቋንቋቸው እንግሊዘኛ ካልሆነላቸው ተንከባካቢዎች መካከል ብዙዎቹ ከትምህርት በኋላ የልጆቻቸውን አካዴሚያዊ ስኬት በቤት ስራ ድጋፍ፣ በእንግሊዘኛ ቋንቋ በመማር እንዲሁም ከእኩዮቻቸው እና አስተማሪዎች ጋር ያለው ግንኙነት እንዴት እንደሚደግፍ አፅንዖት ሰጥተዋል ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው ቤተሰቦች የመጡ እንክብካቤ ሰጪዎችም ከመደበኛ ትምህርት በኋላ የሚደረጉ ፕሮግራሞች በልጆቻቸው የትምህርት እና ማህበራዊ ክህሎት እድገት ውስጥ ስላለው ሚና ተመሳሳይ አስተያየቶችን ሰጥተዋል። በተጨማሪም በርካታ እንክብካቤ ሰጪዎች ከመደበኛ ትምህርት በኋላ የሚደረጉ ፕሮግራሞች ልጆቻቸው በሥራ እንዲጠመዱ እና ቤት ውስጥ የሚኖረውን አላስፈላጊ እና ያልተፈለገ የስክሪን ጊዜ እንዲገደብ ማድረጉን አጋርተዋል።

# የOST ማስፋፊያ ሪፖርት ማጠቃለያ

# የOST ማስፋፊያ ጥናት ምክረ ሀሳቦች

## እኤ 2025

የገንዘብ ድጋፍ የፕሮግራም ቦታዎችን ለማስፋፋት እና ክፍተቱን ለመቀነስ ወሳኝ ቢሆንም፣ መዋቅራዊ የሥርዓት ለውጦችን ማምጣት ግን ጊዜ የሚወስዱ እና የተቀናጁ ስልቶችን መጠቀም ይጠይቃል። ስለሆነም ባለድርሻ አካላቱ የችግሮቹን መንስዔዎች ከሥር መሠረታቸው ለመፍታት የሚያስችሉ አምስት ምክረ ሀሳቦችን አቅርበዋል፦

1. መዋቅራዊ የሥርዓት ስብጥር መገንባት
2. ፍትሃዊነትን ያማከለ ምዝገባ
3. ቦታ ማጋራት
4. ልዩ ፍላጎቶች ያሏቸውን ተማሪዎች መደገፍ
5. ጠንካራ የOST የሥራ ኃይል

እነዚህ ምክረ ሀሳቦች እና ተጓዳኝ ስልቶች ዓላማቸው ውጤት እያስገኙ ያሉትን አሠራሮች ማጠንከር፣ እያስገኙ ያልሆኑትን ደግሞ የገንዘብ ድጋፍ ሲገኝ የማስፋፊያ ሥራዎቹ በተሳካ እና ዘላቂነት ባለው መልኩ እንዲካሄዱ ለማረጋገጥ መለወጥ ነው። እነዚህ ምክረ ሀሳቦች በአስፈላጊነት ቅደም ተከተል አልተዘረዘሩም፣ ሊሠራባቸውም የሚገባው በተመሳሳይ ሰዓት ነው።

**ምክረ ሀሳብ #1:**

**መዋቅራዊ የሥርዓት ስብጥር መገንባት**

## የሕፃናትን፣ ወጣቶችን እና ቤተሰቦችን ደኅንነትን ማዕከል አድርጎ ለመሥራት የሚያስችሉ ግቦችን ማዳበር እና በCPS እና OST ሥርዓቶች መካከል ያለውን ስብጥር ማሻሻል።

### ስልቶች

- የመደበኛ ትምህርት እና ከመደበኛ ትምህርት በኋላ የሚደረጉ ሠራተኞች አንድ ላይ በትብብር እንዲሠሩ ለማድረግ የሚያስችል የጋራ መሪ ቃል ወይም ዓላማ ማዘጋጀት።
- የጋራ ባለቤትነት እና ቁርጠኝነት ስሜትን ለማዳበር በትምህርት ቤት እና ከትምህርት በኋላ የወጣቶችን እድገት የሚያበረታቱ የጋራ ግቦችን እና የትምህርት አሰጣጥ ውጤቶችን ማዘጋጀት።
- በትምህርት ቤቶች እና ከትምህርት በኋላ በሚደረጉ ፕሮግራሞች መካከል ቅንጅትን የሚያነቃቁ ሥርዓቶችን፣ መዋቅሮችን እና ቦታዎችን መፍጠር።
- ስትራቴጂዎቹን በመተግበር እና በጋራ ግቦች ላይ በመሥራት ረገድ የእያንዳንዱን ድርጅት አስተዋጽዖ እና ሚና መለየት።

**ምክረ ሀሳብ #2:**

**ፍትሃዊነትን ያማከለ ምዝገባ**

**ተጨማሪ ቦታዎች መኖራቸውን እና መገለል ላጋጠማቸው ተማሪዎች እና ቤተሰቦች ተደራሽ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ፍትሃዊነትን ግቡ ያደረገ የማስፋፊያ ስትራቴጂ መንደፍ።**

---

## ስልቶች

- በፕሮግራሙ መሳተፍ የሚፈልጉ ልጆች እና ቤተሰቦች በሙሉ መሳተፍ እንዲችሉ ማድረግን ግቡ አድርጎ የተነሳ የማስፋፊያ ሥራ መሆኑን ለማረጋገጥ ፍትሃዊነትን ያማከለ፣ አገልግሎቱን ለሁሉም ተደራሽ የሚያደርግ የታለመ አካሄድ መጠቀም።
- በOST ፕሮግራሞች ለምዝገባ፣ ለቅበላ እና ለwaiting pools ሂደቶች በሥራ ላይ የሚውሉ አሠራሮች ወጥነት እንዲኖራቸው ማድረግ።
- ለሁሉም ፕሮግራሞች "Common App ሥርዓት" የማበጀት አካሄድን በመጠቀም አንድ ወጥ የምዝገባ እና waiting pool ሥርዓት መፍጠር።
- ምደባ የሚፈልጉ ተማሪዎችን ለመለየት እና ቤተሰቦቻቸው እንዲመዘገቡ፣ ሂደቱን እንዲከታተሉ እና የገንዘብ ድጋፍ እንዲያቀናጁ የሚያግዝ የድጋፍ ሥርዓት መፍጠር።
- የአገልግሎት አቅርቦቱ እንዲሻሻል የአሠራር ሂደቶችን እና ሥርዓቶችን ለማስተካከል የምዝገባ ሥርዓቶችን አሠራር በተመለከተ ቀጣይነት ያለው የቤተሰብን እና የእንክብካቤ ሰጪን አስተያየት ለመሰብሰብ የሚያስችል ዘዴ ማመቻቸት።

ምክረ ሀሳብ #3:

ቦታ ማጋራት

## በከተማው ውስጥ ብዙ ልጆችን ማገልገል እንዲቻል በCPS ትምህርት ቤቶች እና OST ፕሮግራሞች መካከል ያለውን የቦታ ማጋራት አሠራር ማሻሻል።

### ስልቶች

- የቦታ ማጋራት አሠራሮችን፣ ስምምነቶችን፣ ልምምዶችን፣ መዋቅሮችን እና ማበረታቻዎችን መፍጠር፤ በእያንዳንዱ ሕንፃ ውስጥ በትምህርት ቤቶች እና ከመደበኛ ትምህርት በኋላ በሚደረጉ ፕሮግራሞች ሠራተኞች እና አመራሮች መካከል የቦታ ፍላጎቶችን እና አጠቃቀምን የሚያስተባብር አንድ ግለሰብ መመደብ።
- የቦታውን “ማህበረሰባዊ” ገጽታ ማሳደግ እና ሁሉንም የትምህርት ቤት ቦታ የጋራ የተማሪዎች ቦታ ማድረግ።
- በOST እና በትምህርት ቤት አስተማሪዎች መካከል አዎንታዊ፣ የተቀናጀ እና የበለጠ የተሰባጠረ የሥራ ግንኙነትን ማዳበር።
- ለOST ፕሮግራሞች እና ማስፋፊያ ሥራው የሚሆኑ ተጨማሪ ቦታዎችን መለየት።

**ምክረ ሀሳብ #4:**

**ልዩ ፍላጎቶች ያሏቸውን ተማሪዎች መደገፍ**

**ከመደበኛ ትምህርት በኋላ የሚደረጉ ፕሮግራሞች ልዩ ፍላጎቶች ላሏቸው ተማሪዎች ፍትሃዊ ተደራሽነት እንዲኖራቸው እና በፕሮግራሞቹ ውስጥ የሚኖራቸው ተሞክሮም አዎንታዊ እንዲሆን ማድረግ።**

## ስልቶች

- የአካል ጉዳተኞችን መብት የሚጠብቁ፣ የሚያስከበሩ እና ተሳትፎ የሚያጠናክሩ ሥራዎችን መሠረት አድርጎ መሥራት። በትምህርት ቤት፣ ከመደበኛ ትምህርት በኋላ በሚደረጉ ፕሮግራሞች እና በቤተሰብ የሚቀርቡትን እንክብካቤዎች እና ድጋፎች ለማቀናጀት ልጅን ያማከለ ሞዴል መጠቀም።
- ልዩ ፍላጎቶች ያሏቸው ተማሪዎች የሚኖራቸውን "ፍላጎቶች" ጠልቆ በመረዳት እና እነዚያን ፍላጎቶች ለማሟላት የግንኙነት ሥራን፣ የመረጃ ማጋራት ሥራን እና individualized education plan (የግለሰባዊ ትምህርት እቅድ፣ IEP) ተደራሽነትን ጨምሮ ፕሮግራሞች/ፖሊሲዎች/ሽርክናዎች/ድጋፎች ማዘጋጀት።
- ልዩ ፍላጎት ላሏቸው ልጆች በቂ ድጋፍ ለመስጠት አግባብነት ያላቸው መረጃዎች እና አገልግሎቶች መኖራቸውን ማረጋገጥ (ለምሳሌ የልጅ ለአስተማሪ ምጣኔን በከፍተኛ ሁኔታ መቀነስ፣ በቂ የሰው ኃይል አቅርቦትን ማረጋገጥ፣ ተስማሚ ቦታ እንዲኖር ማድረግ፣ የበለጠ ሰፊ የሰው ኃይል ሞዴሎችን መንደፍ።)
- ሁሉም ሠራተኞች ልዩ ፍላጎት ያሏቸውን ልጆች ለመደገፍ የሰለጠኑ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ማበረታቻዎችን፣ መስፈርቶችን እና እድሎችን መፍጠር፤ በሁለቱም ሥርዓቶች ውስጥ ላሉ ሠራተኞች ሙያዊ እድገትን ለማቅረብ CPS እና OST በተቀናጀ መልኩ እንዲሠሩ ማድረግ።
-

**ምክረ ሀሳብ #5**

**ጠንካራ OST የሥራ ኃይል**

## ከፍተኛ ጥራት ያለው አገልግሎት ማቅረብ እና ከመደበኛ ትምህርት በኋላ ለሚቀርቡ ፕሮግራሞች ተጨማሪ ፍላጎቶችን ማስተናገድ የሚችል የተረጋጋ፣ ቀዳሚ የወጣቶች ባለሙያ የሥራ ኃይል መገንባት።

### ስልቶች

- ሠራተኞችን ለመሳብ እና ለማቆየት አስተዳደራዊ ሥርዓቶችን፣ ጥቅማ ጥቅሞችን/ክፍያዎችን እንዲሁም የሥራ ባህል/የሥራ-ሕይወት ሚዛናዊነትን ማሻሻል።
- ባለሙያ ማብቂያ መንገዶችን እና የተቀናጀ የሠራተኞች እድገትን መገንባት።
- በትምህርት ቤቶች እና ከመደበኛ ትምህርት በኋላ በሚደረጉ ፕሮግራሞች መካከል ጠንካራ አጋርነትን ማጎልበት።
- ተግባራዊ መሆን ሲችል እና ሲኖርበት፣ ሠራተኞች ከቅጥር ጥቅማ ጥቅሞች ተጠቃሚ መሆን የሚችሉበትን የሙሉ ጊዜ ተቀጣሪ ሁኔታ የሚያመቻች የሠራተኞች ሞዴል መጠቀም

# ተቀላቀሉን፡፡



@agendacambridge

www.agendaforchildrenost.org

khari@agendaforchildrenost.org

susan@agendaforchildrenost.org